ሊድ ስለመኖሩ ለማወቅ ውሃን መመርመር፦ ጥያቄዎች እና መልሶች

1. በ CPS ሕንፃዎች ላይ ውሃን ለመመርመር ታሪካዊ የአሠራር ሂደቱ ምን ይመስላል?
በእያንዳንዱ ዓመት፣ CPS ሊድ በውሃ ውስጥ መኖሩን ለማወቅ ከኬምብሪጅ የውሃ አቅርቦት መምሪያ ጋር በመተባበር የሚጠጣ ውሃ ምርመራዎችን ሲያደርግ ቆይቷል። የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን [Environmental Protection Agency (EPA)] በውሃ የሊድ ምርመራ ላይ የእርምጃ ደረጃው (ማለትም እርምጃ መወሰድ ያለበት ደረጃ) በአንድ ቢሊዮን 15 ክፍሎች (15 ማይክሮግራም በአንድ ሊትር ወይም .015 ሚሊግራም በሊትር) መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል። ላለፉት አሥር ዓመታት ሁሉም የምርመራ ውጤቶች የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን [Environmental Protection Agency (EPA)] ካስቀመጠው ገደብ ያላለፉ ቢሆንም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ ባሉ በጣት የሚቆጠሩ የሚጠጣ ውሃ ማስተላለፊያዎች/ መጠቀሚያዎች ላይ ግን ይህ አልተከበረም ነበር። እነዚህ መጠቀሚያዎች ለእርምጃ ደረጃ ከተቀመጠው ገደብ በላይ አልፈው ሲገኙ፣ በሌላ ተተክተዋል እና ከዚያ በኋላ ግን ምንም ተጨማሪ ችግሮች አልተገኙም።

2. በዚህ ዓመት በሁሉም የ CPS ትምህርት ቤቶች ለምን ሁሉንም ቧንቧዎች እና መሥመሮች ለምን እንዲመረመሩ ተወሰነ?
ይህ ውሳኔ በውሃ ውስጥ ስላለ ሊድ የሚያስከትላቸው ችግሮች እንዲሁም ከታሸገ የፕላስቲክ ውሃ ይልቅ የቧንቧ ውሃ ለተለያዩ የጤና እና አካባቢያዊ ምክንያቶች ተመራጭ የሚሆንባቸው ምክንያቶች ላይ ያለው ግንዛቤ እየጨመረ መምጣቱን የሚያንፀባርቅ ነው።

3. በ CPS ሕንፃዎች ውስጥ በሚጠጣ ውሃ ውስጥ ሊድ መኖር አሳሳቢ ደረጃ ላይ ደርሷል?
አልደረሰም። ባለፉት 10 ዓመታት የተደረጉ ምርመራዎች ውጤቶች በ CPS ሕንፃዎች ውስጥ ያለው የሚጠጣ ውሃ በአጠቃላይ ሲታይ ለደኅንነት አስተማማኝ እንደሆነ ያሳያሉ። የእኛ ጠቅለል ያለ ሁሉን አቀፍ ምርመራ አንዳንድ በተንተን ብለው የሚገኙ ቧንቧዎች በአዲስ መተካት እንዳለባቸው የሚያሳይ ቢሆንም በኬምብሪጅ እና በ CPS ያለው የሚጠጣ ውሃ የጥራት ደረጃው በአጠቃላይ ሲታይ ከፍተኛ የጥራት ደረጃ እንዳለው ያሳያል።

4. ጠቅለል ያለው ሁሉን አቀፍ የሊድ ምርመራው የተደረገው መቼ ነበር?
በ 2015-16 የትምህርት ዘመን የመጨረሻዎቹ ሁለት ሳምንታት፣ በቅርብ ጊዜ ከታደሱት Cambridge Rindge እና Latin ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሕንፃዎች እንዲሁም አዲስ ከተገነባው የ Dr. Martin Luther King, Jr. / Putnam Avenue Upper School ሕንፃ በስተቀር በሁሉም ትምህርት ቤቶች ሕንፃዎች ላይ ከሚገኙ ሁሉም ቧንቧዎች ላይ የውሃ ናሙናዎች ተወስደው ነበር። እነዚህ ሁለት ትምህርት ቤቶች በሴፕተምበር ወር ውስጥ ምርመራ ይደረግባቸዋል።

5. የምርመራ አደራረጉ አካሄድ እንዴት ነበር?
በኬምብሪጅ የውሃ አቅርቦት መምሪያ የቤተሙከራ (ላቦራቶሪ) ሠራተኞች የቅርብ ክትትል ሥር የ CPS ተቋማት መምሪያ አባል ከእያንዳንዱ ቧንቧ እንዴት ተገቢነት ያለውን የውሃ ናሙና መውሰድ እንዳለበት መመሪያ ተሰጥቶት ነበር። ውሃው በቧንቧዎች ውስጥ ሳይንቀሳቀስ ለ 12 ሰዓታት መቆየቱን ለማረጋገጥ እንዲቻል ሁሉም ናሙናዎች ጠዋት በማለዳ ከምንም ነገር በፊት እንዲወሰዱ ተደርገው ነበር። ከ CPS ወደ የኬምብሪጅ የውሃ አቅርቦት መምሪያ ናሙናው በሚተላለፍበት ጊዜ ጥብቅ የሆነ የጥበቃ አደራረግ የዕዝ ሠንሠለት ተግባራዊ ተደርጓል።

6. አሁን ምርመራው እንደ መደረጉ፣ በአንዳንድ ቧንባዎች ላይ ያለው የሊድ የመኖር ደረጃ ምን ይመስላል።
በእኛ ሕንፃዎች ላይ ያለው ውሃ EPA ያስቀመጣቸውን መስፈርቶች እንደሚያሟላ እንደ ማወቃችን፣ በአሮጌ ቧንቧዎች እና ማስተላለፊያዎች ላይ ሊድ ወደ ውሃ ውስጥ ገብቶ ብክለትን ሊፈጥር የመቻሉ ዕድል ከፍተኛ ነው። በርካታ አሮጌ ቧንቧዎች የነሐስ ንጥረነገሮችን እንዲይዙ ተፈቅዶላቸው ነበር። ነሐስ የንጥረ ነገር ዓይነቱ አሎይ [alloy] የሚባል ሲሆን—የሚታሎች ቅልቅል ነው—ይህም መዳብ፣ ዚንክ እና ሊድን ሊያካትተ ይችላል። በመሆኑም ለችግሩ ተጠያቂው አሮጌዎቹ ዕቃዎች የመሆናቸው ዕድል ከፍተኛ ነው።

7. ብክለቱ ያለባቸው ቧንቧዎች/የሚጠጣ ውሃ ማስተላለፊያዎች/መሥመሮች አሁንም ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው?
አይደለም። ሁሉም ሲመረመሩ በቢሊዮን 15 ክፍሎች ወይም ከዚያ በላይ ያላቸው ቧንቧዎች አገልግሎት እንዳይሰጡ ተደርገዋል እንዲሁም ዕቃዎቹ ሙሉ በሙሉ በአዲስ እስከሚተኩ ድረስ ከአገልግሎት ውጭ እንደሆኑ ይቆያሉ በተጨማሪም ውሃው EPA ባስቀመጠው መመሪያዎች ተገዢ መሆኑን ለማረጋገጥ ቧንቧዎች እንደገና ምርመራ ተደርጎባቸዋል።

8. ዕቃዎቹን በአዲስ መተካቱ ችግሩን ሳይፈታው ቢቀርስ?
ተጨማሪ ምርመራ ሲደረግ ውሃው ከእርምጃ ደረጃው በላይ የሚያልፍ መሆኑን ከቀጠለበት የሕንፃው የውሃ አቅርቦት መሠረተ ልማት ሊድ ሙሉ በሙሉ እስከሚወገድ ድረስ በተደጋጋሚ ምርመራ ይደረግለታል። ዕቃዎች ምርመራው የ EPA መስፈርቶች ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ መሆናቸውን ምርመራው እስከሚጠቁም ድረስ ከአገልግሎት ውጭ ይሆናሉ።

9. የተበከሉ ሁሉም ቧንቧዎች/መሥመሮች ትምህርት ቤት በሚጀመርበት ጊዜ ወደ አገልግሎት መስጠት ይመለሳሉ?
ግቡ ያ ነው። ይህንን የማብቂያ የመጨረሻ ቀን ሳናከብር ብንቀር፣ ሁሉም ተማሪዎች እና ሠራተኞች ሊጠጣ ለሚችል ውሃ በቂ መዳረሻ እንዳላቸው ለማረጋገጥ አስፈልጊ የሆኑ እርምጃዎችን እንወስዳለን።

10. ሁሉም ቧንቧዎች እና የውሃ ፍሳሽ መሥመሮች በ EPA ያስቀመጣቸው መስፈርቶች ውስጥ ተገዢ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ምን እርምጃዎች እየተወሰዱ ነው?
ሁሉንም ቧንቧዎች ቀጣይነት ባለው መልኩ ለመቆጣጠር ይበልጥ ጠቅለል ያለ ሁሉን አቀፍ የምርመራ ፕሮግራም በመዘጋጀት ላይ ነው። ይህ ፕሮግራም ለትምህርት ቤቱ ኮሚቴ በዚህ ፋል (በልግ) ይቀርብለታል።